# በሰማይ ጠቀስ የሕዝብ መኖሪያ ቤቶች ውስጥ ለሚኖሩ እና ወደ ሌላ ቦታ ለማይዛወሩ ተከራዮች በተደጋጋሚ የሚጠየቁ ጥያቄዎች

20 ሴፐተምበር 2024

Amharic | አማርኛ

## ዛሬ የታወጀው ምንድን ነው?

የቪክቶሪያ መንግስት የሆምስ ቪክቶሪያ የትልቁ መኖሪያ ቤት ግንባታ (Big Housing Build) አካል ሆነው እንደገና የሚገነቡትን ቀጣይ ቦታዎች አስታውቋል። እነዚህ ቦታዎችም የሚከተሉት ናቸው፡-

- **139 Highett Street, Richmond**
- **259 Malvern Road, South Yarra**
- **6 & 8 Anderson Court, Richmond**
- **1 - 5, 7 & 9 Williams Court, Richmond**
- **111, 119 & 127 Elizabeth Street, Richmond.**

## ይህ ማስታወቂያ ለእኔ ምን ማለት ነው?

በቤተሰብዎ ላይ ወድያውኑ የሚደርሱ ምንም ዓይነት ተጽእኖዎች የሉም።

በ2051 በሜልበርን ዙሪያ ያሉትን 44 ሰማይ ጠቀስ የሕዝብ መኖሪያ ቤቶች እንደገና የመገንባቱ እቅድ ላይ ምንም ለውጦች የሉም።

## የእኔ ፎቅ መልሶ ግንባታ የታቀደው መቼ ነው?

**ከጁላይ 2026** በፊት ወደ ሌላ ቦታ እንዲዛወሩ አይገደዱም።

የፕሮጀክቱ ቀጣይ ደረጃ ሲወሰን ከተደጋጋሚ ማስታወቂያ ጋር ተጨማሪ መረጃ እንሰጥዎታለን።

## የእኔ ፎቅ ለመልሶ ግንባታ መድረሱ ሲታወጅ ምን ይሆናል?

ፎቅዎ ለመልሶ ግንባታ መድረሱ ሲታወጅ የሆምስ ቪክቶሪያ ከቦታ ወደ ቦታ የሚያዛውር ቡድን ለእርስዎ ተስማሚ የሆነ የመኖሪያ ቦታ ለማግኘት ከእያንዳንዱ ቤተሰብ ጋር ይሰራል።

ይህ ጊዜ ይወስዳል፣ እና እርስዎ ወዲያውኑ እንዲንቀሳቀሱ አይጠበቅብዎትም።

## በእኔ ቦታ ላይ ምንድነው የሚገነባው?

ለአዲሶቹ ቤቶች የተነደፉ ንድፎች ገና አልተጠናቀቁም ነገር ግን ዘመናዊ እና ደህንነቱ የተጠበቀ ማህበራዊ መኖሪያ ቤትን ያካትታል።

በንድፎቹ ላይ ግብረ መልስ የመስጠት እድል ይሰጥዎታል።

## በሌሎች ቦታዎች ላይ ምን እየሆነ ነው?

በ120 Racecourse Road እና በ12 Holland Court፣ **Flemington/ፍሌሚንግተን**፣ 33 Alfred Street፣ **North Melbourne/ሰሜን ሜልበርን** የማዛወር ስራ አሁን እየተካሄደ ይገኛል።

ተከራዮች በተዛወሩባቸው በሁለቱ ሰማይ ጠቀስ ቦታዎች፣ ማለትም በ20 Elgin Street እና በ141 Nicholson Street, **Carlton/ካርልተን** ላይ የመልሶ ግንባታ ሥራ በቅርቡ ይካሄዳል።

## ተጨማሪ መረጃ እንዴት ማግኘት እችላለሁ?

ስለ ታላቁ የቤት ግንባታ (Big Housing Build)፣ ሰማይ ጠቀስ ፎቆችን መልሶ ለመገንባት ስላለው እቅድ የበለጠ መረጃ ለማግኘት እና ለመረዳት፡-

- በማህበረሰብ ጊዜያዊ ስብሰባ ብቅ ብለው ይሳተፉ
- የአካባቢዎን የቤቶች ቢሮ ያነጋግሩ
- ከአከባቢዎ የቤቶች ቢሮ ጋር ለመገናኘት በ 1800 716 866 (ከጠዋቱ 9 ሰዓት - ከሰዓት በኋላ 5 ሰዓት፣ ከሰኞ እስከ አርብ) ይደውሉ። አስፈላጊ ከሆነ አስተርጓሚዎች አሉ
- ወደ enquiries@homes.vic.gov.au ኢሜይል ያድርጉ።